ልብስ እና ምላስ

ዳንኤል ክብረት

በአንድ ጫካ ውስጥ አንድ አስቸጋሪ ዘንዶ ይኖር ነበር፡፡ አዘንዶው መኖሪያ ባሻገር ልዩ የኾነ የወርቅ ማውጫ ቦታ ነበር፡፡ የአገሬው ሰዎች ከዚህ ወርቅ መጠቀም ይፈልጉ ነበር፡፡ የዘንዶው ነገር ግን አስቸጋሪ ኾነባቸው፡፡ በመጨረሻ ሽማግሌዎቹ መካሩ እና ዘንዶውን ለማነጋገር ግብር ይዘው ሄዱ፤ ዘንዶውም ወርቁን ለመውሰድ «በእውነት ለፈጣሪያቸው ያደሩ እውነተኛ መንፈሳውያን መሪዎች አንደሚያስፈልጉ፤ አነርሱን መርጠው መላክ ከቻሉ አንዳች ጉዳት ሳያደርስባቸው ወርቁን መውሰድ እንደሚችሉ ነገራቸው፤ ሽማግሌዎቹም በሰሙት ነገር ተደስተው ለሕዝቡ ሐሳቡን አቀረቡ፤ ሕዝቡም «በዚህ የሚኾኑ ሰዎችማ አይጠፉም» ብለው ከአስላምም ከክርስቲያንም ወገን የኾኑ የየአምነቱን መሪዎች መርጦ ወርቁን እንዲያመጡ ላካቸው፡፡ አነርሱም የአምነት መሪነታቸው የሚታወቅበትን ልብስ ለብሰው ወደ ዘንዶው ተጓዙ፡፡ ሕዝቡ በመሪዎቹ ስለ ተማመነ ወርቁን በተስፋ መጠበቅ ጀመረ፡፡

ሰዓታት አልፈው ቀናት፤ ቀናትም አልፈው ሳምንታት ተተኩ፤ የካይማኖት አባቶችም ኹኑ ወርቁ አልመጣም፡፡ ሳምንታቱ ወደ ወራት ሲቀየሩ ግን ሕዝቡ ጥርጣሬ ውስጥ ወደቀ፤ ሽማግሌዎቹም ከሕዝቡ ጋራ መክረው ወደ ዘንዶው ተጓዙ፡፡ ዘንዶው ወዳለበት ቦታ ሲደርሱ ጥቂት ሲቀራቸው የአነዚያን የአምነት መሪዎች ልብሶች አንድ አካባቢ ወዳድቀው አገኟቸው፤ ከልብሶቹ አጠገብም የሁሉም ሽማግሌዎች ምላሶች ተሰባስበው ታቀምጠዋል፡፡ በዚህ መካከል ዘንዶው ከበላቱ (ከማደርያው) ወጥቶ መጣ፡፡ አነዚያም ሽማግሌዎች «ከእስላም ከክርስቲያን የተመረጡ የአምነት አባቶቻችንን ልከን ነበር፤ እስከ አሁን ግን አልተመለሱም፡፡ ኹኔታቸው ቢያሳስበን እኛ መጣን» ሲሉ ጠየቁት፤ ዘንዶውም «እኔ መንፈሳውያን መሪዎችን ላኑ አልኳችኹ እንጂ መች ልብስ እና ምላስ ላኑ አልኳችኹ፡፡ እነዚህኮ ምላሳቸው እና ልብሳቸው ብቻ ነው መንፈሳዊ፤ በሌላው ነገር ከምእመናኖቻቸው የባሱ ናቸው፡፡ እኔም መንፈሳዊ የኾነው ምላሳቸው እና ልብሳቸው ብቻ በመኾኑ እርሱን አልነካኹትም፤ የቀረውን ግን በልቼዋለኹ» አላቸው፡፡

ኢትዮጵያውያን ለእምነት ተቋሞቻቸው ልዩ ቦታ አላቸው፡፡ አብዛኛው የአገሪቱ ሕዝብም የሁለቱ ታላላቅ እምነቶች (የክርስትና እና የአስልምና) አማኝ ነው፡፡ በየቤተ እምነቱ ፈጣሪውን በየዕማኖት ለማማኘት የሚተጋውን ምእመን ከአወሮፓ እና አሜሪካ ምእመን ጋራ ስናነጻጽረው ልዩነቱ የትየለሌ ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን ለየእምነታቸው ገንዘባቸውን፤ ጊዜያቸውን እና ሕይወታቸውን ለመሠዋት የማይደራደሩ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ እንደ ምግብ እጥረት የአማኝ እጥረት አልገጠማትም፡፡ የቸገራት ሌላ ነው፡፡

አሁን የአገራችን ሕዝብ ታራኩን እና አንድነቱን ጠብቆ፤ ልዩነቱን አክብሮ ነገር ግን አንድ በሚያደርገኑ ገመዶች ተሳስሮ፤ በእምነቱ ጸንቶ በምግባሩ በርትቶ፤ ነገር ግን ከድህነት ዘንዶ፤ ከመሐና ዘንዶ «እኔን ብቻ ይድላኝ» ከሚለው ዘንዶ፤ ከዘረኝነት እና ከጎጠኝነት ዘንዶ፤ ከኗላ ቀርነት ዘንዶ፤ ከምግብ ዕጦት እና ከነሮ ውድነት ዘንዶ ባሻገር

ያለውን የብልጽግና እና የእኩልነት፤ የፍትሕ እና የሥልጣኔ፤ የመንፈሳዊ ብቃት እናርቴዕነት ወርቅ የሚያመጣለት መንፈሳዊ መሪ ነው የቸገረው፡፡

በሕዝብ መካከል ቅራኔ ሲፈጠር በአባትነት እና በሽምግልና፤ በአገር መሪዎች መካከል መቃቃር ሲፈጠር በታሳቅነት እና በገልጓተኛ አስታራቂነት፤ በእምነት ተቋማት መካከል ያለው ልዩነት ወደ ጠብ ሲያድግ በምክክር እና በመግባባት፤ ፍፍትሕ እና የርትዕ መንደል ሲያጋጥም በመገሠጽ እና የሕዝብን ብሶት በማሰማት፤ ሕዝቡ ሲያገኘው የሚፈልገውን ወርቅ ዘንዶውን ተሻግሮ የሚያመጣለት መንፈሳዊ መሪ ነው የናፈቀው፡፡

ምንም እንኳን የአንደኛው እምነት መሪ ቢኾን፤ የሚያምነብት እና የተሾመበት፤

የሚያገለግለው እና የሚጸናው በእምነቱ ቢኾንም፤ በቅንነቱ እና በደግነቱ፤ በቸርነቱ እና

በእስተዋይነቱ፤ በትምህርቱ እና በምክሩ፤ ለአገር እና ለወገን በሚያደርገው ድንበር ተሻ

ጋሪ አገልግሎት፤ ሰው ለኾነ ሁሉ በሚያበረክተው ሰብእዊ ተግባር፤ ሁሉም ለሚሻቸው ነጻነት እና እኩልነት፤ ሰፍትሕ እና ለሰብአዊ መብቶች መከበር ድምፁን በማሰማቱ የሌሎች እምነቶች ተከታዮች እንኳን የሚያከብሩት እና የሚወዱት፤ ፖለቲከኛ

ኾም የሚለሙት እና የሚፈሩት ዘንዶውን የሚሻገር መሪ ናፍቆታል፡፡

የሰው ችግር የሚታያቸው፤ የድኻ እንባ የሚገዳቸው፤ ቤተ እምነቶቻቸው ሲፈርሱ፤ አገልጋዮቻቸው ሲራቡ፤ ሕዝባቸው ኑሮ ሲከብድበት የሚጨንቃቸው እና ሲያቀሱለት የሚተጉ የእምነት መሪዎችን ይህ የዋህ ሕዝብ መቼ ነው የሚያገኘውቅ ወይስ እንደነዚያ

ሰዎች ልብሱን እና ምላሱን ብቻ ነው ለማማኘት የታደለው? ጆን ፖልን ከቫቲካን፤ ዴዝ ሞንድ ቱቱን ከደቡብ አፍሪካ፤ ማርቲን ሉተር ኪንግን ከአሜሪካ፤... ኢትዮጵያውያን አድርጎ ማን ባመጣልን? ጎዳና የሚያድር ድኻ ሕዝባቸው ላይ ሁለት እና ሦስት ቪላ ቤቶች አየሠሩ «እንቁልልጮሽ» የሚሉ፤ «የሰማዩን ቤት ይሠሩልኛል» ብሎ ከሚያስባቸው መንፈሳዊ

መሪዎች በራሱ ገንዘብ የሠሩትን ቤት የሚያከራይ፤ ከድኻዋ መበለት በተሰበሰበ ገንዘብ የሚልዮን ብሮች መኪና ከውጭ አገር የሚያስመጡ፤ እኛ የፈጣሪ ወገን ናቸው ብለን

ስናስብ፤ አነርሱ ግን ለታላላቁ ማዕርግ ከደረሱ በኋላ እንኳን አጥንት እና ጉልጥምት አየቆጠሩ፤ ወገን እና ዘመድ አየበሰበሱ የቤት ልጅ እና የውጭ ልጅ ብለው የሚለዩ፤

የማይፈጽሙትን የሚያስተምሩ፤ በማያምኑበት የሚኖሩ፤ ኤዲፕስ ንጉሥ «ንጉሥነት እንጀራዬ ነው» እንዳለው ቅጽበኛ፤ ቅስና፤ ምንኩስና፤ ፓስተርነት፤ መጋቢነት፤ ዘማ ሪነት፤ ቃዲነት፤ ዑላማነት፤ ሐጂነት «አህል ውጋቸው» ብቻ የኾነ፤ «መንፈሳውያን» መሪዎች የየዘመኑ፤ የየፖለቲካው፤ የየርእዮተ ዓለሙ ዘንዶ አየበላቸው፤ ልብሳቸው እና ምላሳቸው ብቻ የሚተርፈን ከኾነ ወርቁን ማን ያምጣልን?

አለቃ ገብረ ሐና የአቡነ ሐራ ድንግል ገዳም አለቃ እያሉ በአካባቢው ድርቅ ገባ፤ ገበሬውም ተራበ፤ አለቃም የገዳሙን ገንዘብ አወጡና ገበሬዎቹን ሰብስበው «አንኑ በዚህ

አህል ሽምታችኹ ብሉ፤ ደግሞም ተግታችኹ ጸልዩ፤ በኋላ አህል ስታገኙ ትከፍላላችኹ»ብለው ገንዘቡን አከፋፈሉት፡፡ በዚህ ምክንያት ተከስሰው አዲስ አበባ ከአፈ ንጉሥ ነሲቡዘንድ ቀረቡ፡፡ እርሳቸውም «እንዴት የገዳሙን ገንዘብ ለገበሬ ያከፋፍሉታል?» ተብለው ቢጠየቁ «አቡነ ሐራ ልጅ አይድሩብት፤ ወላጆቻቸውን አይጦሩበት፤ ልጆቻቸውም ወላጆቻቸውም እነዚህ ገበሬዎች ናቸው፡፡ ሲራቡ ብሰማቸው ያስመልሷግኖል እንጂ አያስ ቀጣኝም» ብለው ተሟገቱ፡፡ አፈ ንጉሥ ግን ጥፋተኛ ናቸው ብለው ፈረዱ፡፡ አለቃምለዐፄ ምኒልክ ይግባኝ አሉ፡፡ ምኒልክም ፍርዳቸውን አድንቀው፤ በሥራቸው ሸልመው፤እንጦጦ ራጉኤልን ሾመዋቸዋል፡፡

ሕዝቡ ሲራብ፤ በየገጠሩ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ሲዘጉ፤ መስጊዶች ያለአስተማሪ ሲቀሩ፤ ሕዝቡ በትምህርት ቤት፤ በጤና ጣቢያ፤ በምግብ ዋስትና ዕጦት ሲሠቃይ፤ምነው እንደ አለቃ ገብረ ሐና የሚያስብ ጠፋ? ልብሱ እና ምላሱ ብቻ ነው ማለት ነውመንፈሳዊ የኾነው? መስና እና የአድሏዊ አሠራር መገለጫቸው የኾኑ ያእምነት መሪዎች ካሱን እንዴት አድርገው ስለ መስና እና ስለ ፍትሕ ሊያስተምሩ ይችላሉ? ወገንተኛ ነት እና ዘረኛነት እስከ አጥንታቸው ድረስ የዘለቃቸው የእምነት መሪዎች ከተፈጠሩ እንዴት አድርገው ስለ አንድነት እና ስለ ወንድማማችነት ሊያስተምሩ ብቃቱ ይኖራቸዋል? በሥራቸው የሚገኙትን አገልጋዮች ማንቃት እና ማሠልጠን ያልቻሉ የእምነት መሪዎች እንዴት አድርገው ሕዝብን ለማንቃት እና ለማሠልጠን ይቻላቸዋል? ከምእመናን የሰበሰቡትን ገንዘብ ግብር ባይከፍሉበትም ቢያንስ ግልጽ ሪፖርት ማቅረብ ያልቻሉ የእምነት መሪዎች ስለ ግልጽነት እንዴት ሊመክሩን ይችላሉ?

ይህቺ አገር እንድታድግ፤ እንድትሠለጥን እና ፍትሕ እና ዴሞክራሲ የነገሠባት እንድትኾን፤ ይህች አገር ከመስና እና ከዘርኝነት ከጎጠኛ አድልዎ ነጻ የኾነ አስተዳደር እንዲኖራት፤ ይህች አገር ትክክለኛ የገንዘብ እና የሀብት አያያዝን መንገድ እንድትከተል፤ ይህች አገር ተወያይቶ፤ ተከራክሮእና ተመካክሮ መኖርን ገንዘብ እንድታደርግ፤ ይህች አገር ሥልጣን ሐሳፊነት እንጂ ጥቅም የማግበስበሻ አጋጣሚ የማይኾንባት አገር እንድትኾን፤ ከልብላቸው እና ከምላሳቸው ባሻገር መንፈሳውያን የኾኑ የእምነት መሪዎች ያስፈልጓታል፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ ምስጉን አምላክ እና መምህር ሲኾን ከሕዝብ መካከል

ነው የኖረው፡፡ የሕዝቡን ምግብ በልቶ ሕዝቡን ነው ያገለገለው፡፡ ሰራሱ የሠራውም ኾነ ያሠራው ልዩ ቤተ መንግሥት አልነበረውም፡፡ ነቢዩ መሐመድም ከሕዝብ ጋራ ነውኖኖሩት፤ ሕዝቡን ሲያስተምሩ እና ሕዝቡን ሲመሩ የሕዝቡን ምግብ በልተው የሕዝቡን

መጠጥ ጠጥተው፤ ከሕዝቡ ጋራ አድረው፤ ሕዝቡን እየሰሙ፤ ችግሩንም እየፈቱ ነው፡፡

መሸኘኑ እንደ ቀድሞዎቹ የእምነቶቹ መሥራቾች ዛሬ መንፈሳውያን መሪዎቻችን ሕዝባቸውን ያውቁታል? የሕዝቡን እንጀራ ይበላሉ? ከሕዝብ ጋራ ውሉው ያድራሉ? ሕዝባ

ቸው የሚላቸውን ይሰማሉ? አነርሱ ምኞት ባለው ተሸከርካሪ ሲንፈላለሱ ሕዝቡ ግን በእግሩ ይኳትናል፡፡ አነርሱ በፓሣስ፤ ሕዝቡ ግን ጎጃ ውስጥ ነው የሚኖረው፡፡ አነርሱ በውጭ አገር ሲዝናኑ ሕዝቡ ግን ዳቦ ለመግዛት እየተሰለፈ ነው፡፡ አነርሱ በየግብዣው ሲሠየሙ ሕዝቡ ግን ፍርፋሪ እየለቀመ ነው፡፡ አነርሱ በታላላቅ ሆቴሎች ሲያርፉ ሕዝቡ ግን በመቃብር ቤት ይኖራል፡፡ አነርሱ በዘበኛ እየተጠበቁ ሕዝቡ ግን ከአጥር ውጭ መግቢያ አጥቶ ቆሟል፡፡ ታዲያ እንዴት ይገናኛሉ? የእምነት መሪዎቻችን ቆም ብለው ራሳቸውን የሚገመግመበት ጊዜው አሁን ነው፡፡ መላ ነገራቸው እንጂ ገግግራቸው እና ልብላቸው ብቻ መንፈሳዊ ሊኾን ወርቁን አያመጣልንም፡፡ «ማሞ ሌላ መታወቂያው ሌላ» እንዳይኾንብን እንደ ልብሳቸው ሁሉ ሕይወታቸውም መንፈሳዊ ካልኾነ ከችግር፤ ከመከራ፤ ከሙስና፤ ከዘረኝነት፤ ከሥነ ምግባርብልሹነት፤ ከአድሏዊነት ዘንዶ ባሻገር ያለው ሕዝቡ የሚናፍቀው መንፈሳዊ፤ ማኅበራዊእና ዴሞክራሲያዊ ወርቅ እንደ ናፈቀው መቅረቱ ነው፡፡

ማስታመቂያ